# ዜና አመዝኮ



## በዚህ እትም ውስጥ


**ያታዊና ሥነፆታዊ ልዩነቶችን ማስተማር በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማስወገድ እንደሚረዳ ተገለፀ**

ፆታዊና ሥነፆታዊ ልዩነቶች በየዕለት እንቅስቃሴ ልጆችን ማስተማር ሴቶች ማህበረሰቡ በፈጠራቸው ባህላዊ ፣ ሀይማኖታዊና ልማዳዊ ልዩነት ሳቢያ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙትን ሥነልቦናዊ ፣ አካላዊና ወሲባዊ ጥቃቶች ለማስወገድ እንደሚረዳ ተገለፀ::

*ገጽ 3*

**በአፋር ክልል በጎርፍ አደጋ ተጎጂ ለሆኑ አስፈላጊው ዕርዳታ ቀርቧል**

በአፋር ክልል በዱብቲ ወረዳ ሐምሌ 17 ቀን 1997 ዓ.ም በአዋሽ ወንዝ ሙላት ሳቢያ በተከሰተው የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ ተጎጂ ለሆኑ ወገኖች አስፈላጊው የምግብና የመጠለያ ዕርዳታ ቀርቧል::

*ገጽ 4*

**የዕርዳታ እህል በግለሰብ መጋዘን ሲራገፍ ተያዘ**

ለተረጂዎች እንዲጓጓዝ ከናዝ ት ማዕከላዊ መጋዘን የተጫነ የዕርዳታ እህል ሐምሌ 16 ቀን 1997 ዓ.ም በግለሰብ መጋዘን ሲራገፍ እጅ ከፍንጅ ተይዟል::

*ገጽ 5*



በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 529259
529262
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣ www.dppc.gov.et



የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን፣ ቅፅ 11 ቁጥር 4 ሀምሌ 1997


## ባለፉት ሦስት ወራት ከ 1.1 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የዕርዳታ እህል ተመድቦ ተከፋፍሏል

ከግንቦት እስከ ሐምሌ 1997 ዓ.ም ባሉት ሦስት ወራት ውስጥ በአፋር ፣ በአማራ ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ፣ በጋምቤላ ፣ በሐረሪ ፣ በኦሮሚያ ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፣ በትግራይ ክልሎችና በድሬደዋ መስተዳድር ለሚገኙ የአስቸኳይ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ተረጂዎች በጠቅላላው 1 ሚሊዮን 124 ሺህ 810 ኩንታል በፌዴራል አመዝኮና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት ተልኮ መከፋፈሉ ታውቋል::

ከዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈጻጸምና ክትትል መምሪያ የቀጠናዎች ማስተባበሪያና ቡድን ባገኘነው መረጃ መሠረት በግንቦት ወር 1997 ዓ.ም ከቀረበው 672 ሺህ 800 ኩንታል ውስጥ በኮሚሽኑ 599 ሺህ 480 ኩንታል ፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በኩል



ደግሞ 73 ሺህ 320 ኩንታል ተመድቦ ለተጎጂ ወገኖች ተከፋፍሏል:: ለሰኔ ወር 1997 ከተመደበው 662 ሺህ 150 ኩንታል ውስጥ ደግሞ በኮሚሽኑ 498 ሺህ 480 ኩንታል ፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል 163 ሺህ 670 ኩንታል ተመድቦ መከፋፈሉ ታውቋል:: እንዲሁም ለሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም ከቀረበው 385 ሺህ 860 ኩንታል ውስጥ በኮሚሽኑ 292 ሺህ 100 ኩንታል ፣ በመያድ በኩል 93 ሺህ 760 ኩንታል መመደቡን ከቡድኑ የተገኘው መረጃ አመልክቷል::

## ህፃናትና እናቶችን ለመታደግ በሚደረግ ልዩ የጤናና ሥርዓተ ምግብ አቅርቦት ላይ ያተኮረ ዐውደ ጥናት ተካሔደ

በሀገሪቱ በድርቅ ተጠቂ በሆኑ አካባቢዎች በተከሰተው የምግብ እጥረት ሳቢያ ይበልጥ ተጠቂ ለሚሆኑት እናቶችና ህፃናት ልዩ የጤናና ሥርዓተ ምግብ (Nutrition) ድጋፍ በማድረግ በተለይ በህፃናት ላይ የሚከተለውን ጉዳት ለመቀነስ ታልሞ በተወሰኑ ክልሎች ተግባራዊ እየተደረገ ያለውን የልዩ ድጋፍ ስትራቴጂ (Enhanced Outreach Strategy) አተገባበርና ሂደት የገመገመና ለአንድ ቀን የቆየ ዐውደ ጥናት ሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተካሂዷል::

በዚሁ አንድ ቀን በቆየው ዐውደ ጥናት ላይ እንደተገለፀው ልዩ ድጋፉ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮዎች ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በክልል ጤና ቢሮዎች ፣



አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮዎች ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በክልል ጤና ቢሮዎች ፣ በዩኒሴፍ እና በዓለም ምግብ ኘሮግራም በጋራ በሚካሄደው ኘሮግራም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፣ በትግራይና በሱማሌ ክልሎች የምግብ እጥረት ለሚያስከትለው ጉዳት ይበልጥ ተጋላጭና ተጠቂ ለሆኑት እናቶችና ህፃናት ልዩ የጤና እክብካቤ በማድረግና ችግሩ በነዚህ የህብረተሰቡ ክፍሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት መቀነስ ነው፡፡

በዩኒሴፍ እና በዓለም ምግብ ኘሮግራም አማካይነት በትብብር የሚተገበር ነው፡፡ በዚህ በጋራ በሚካሄደው ኘሮግራም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፣ በትግራይና በሱማሌ ክልሎች ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይኸው በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በትብብር በሦስቱ ክልሎች እየተተገበረ ያለው ልዩ ድጋፍ ዋነኛ ዓላማ የምግብ እጥረት ለሚያስከትለው ጉዳት ይበልጥ ተጋላጭና ተጠቂ ለሆኑት እናቶችና ህፃናት ልዩ የጤና ክብካቤ በማድረግና በተለይ ህፃናቱ የተሟላ አካላዊ ጥንካ እስከሚያገኙ ድረስ አልሚ ምግብ የሚያገኙበትን ስልት በመዘርጋት ችግሩ በነዚህ የህብረተሰቡ ክፍሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት መቀነስ ነው፡፡

የልዩ ድጋፉን ዋነኛ ዓላማ ለማሳካትም በተለይ ተጎጂዎቹ በሚገኙባቸው ተግባራዊ እየተደረገባቸው በሚገኙት ሦስት ክልሎች አበረታች ውጤት መገኘቱ ተጠቅሷል፡፡

ኘሮግራሙ ተግባራዊ እየተደረገባቸው ባሉት ሦስት ክልሎች የተደረሰባቸው ስኬቶች፣ የተገኙ ልምዶች ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሔ ሀሳቦች ከየክልሎቹ በዓውደ ጥናቱ ላይ ተካፋይ በሆኑት ተወካዮች ቀርበው ሠፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ በሂደት ታዩ ተብለው ለቀረቡ ችግሮችም ገንቢ የሆኑ የመፍትሔ ሀሳቦች ተሠንዝረዋል፡፡

በሌላም በኩል ልዩ ድጋፉን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ቁልፍ ተግባራት ናቸው ተብለው በዐውደ ጥናቱ አዘጋጆች በቀረቡ በመረጃ አሰባሰብ ጥራትና ትንታኔ ፣ በሎጂስቲክስና በምግብ አቅርቦት ወሰነ ጊዜ፣ የተጎጂዎች መረጃን በወጉ በመለየት ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወቅታዊ ምላሽ መስጠት በሚሉ ርዕሶች ላይ የቡድን



ውይይት ተደርጎባቸው በአፈጻጸማቸው ላይ በየቡድኖቹና በተሳታፊዎች የቀረቡት የማጠቃለያ ገንቢ ሃሳቦችም በቀጣይ በየደረጃው ለሚካሄደው የልዩ የምግብና የህክምና ድጋፍ ክብካቤ ሁነኛ አስተዋጽዖ እንደሚያበረክት ተመልክቷል፡፡

አካባቢዎች ያሉ የጤና ሠራተኞች በኘሮግራሙ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ማሳደግና ሙያዊ ዕውቀታቸውን በስልጠና ማጠናከር ፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማጎልበት ፣ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ማስፋፋትና ሌሎችም ተዛማጅ ጉዳዮች ትኩረት የሚሹ መሆናቸው በዓውደ ጥናቱ ላይ ተመልክቷል፡፡ ምንም እንኳን ወደፊት ኘሮግራሙን ወደሌሎች ክልሎች ለማስፋፋት ለተያዘው ውጥን ናሙና ኘሮጀክት ከተያዙት ክልሎች ልምድ በመነሳት ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ በአፈጻጸም ሂደት አንዳንድ መሻሻል ያለባቸው ነገሮች ቢኖሩም

በዐውደ ጥናቱ ላይ ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ፣ ከክልል የጤና ፣ የምግብ ዋስትናና አመዝ ቢሮዎች ፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ ከዩኒሴፍ እና ከዓለም ምግብ ኘሮግራም የተወጣጡ ከሀምሳ በላይ የሚሆኑ ባለሙያዎች ተካፋይ መሆናቸው ታውቋል፡፡

# ፆታዊና ሥነፆታዊ ልዩነቶችን ማስተማር በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማስወገድ እንደሚረዳ ተገለፀ

በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን ፆታዊና ሥነፆታዊ ልዩነቶች በየዕለት እንቅስቃሴ ልጆችን ማስተማር ሴቶች ማህበረሰቡ በፈጠራቸው ባህላዊ ፣ ሀይማኖታዊና ልማዳዊ ልዩነት ሳቢያ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙትን ሥነልቦናዊ ፣ አካላዊና ወሲባዊ ጥቃቶች ለማስወገድ እንደሚረዳ ተገለፀ፡፡

ይህ የተገለፀው ለ60 የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ሠራተኞች በፆታና ሥርዓተ ፆታ ፣ በሥርዓተ ፆታና ልማት ፣ በሰብዓዊ መብቶችና በሴቶች መብቶች ላይ ያተኮረ አውደ ጥናት በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የመሰብሰቢያ አዳራሽ ከሐምሌ 19 እስከ ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም በተካሄደው ዐውደ ጥናት ላይ ነው፡፡

በዚሁ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የሴቶች ጉዳይ መምሪያ ጋር በመተባበር ባዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ በጥናታዊ ፅሑፍ አቅራቢዎቹ እንደተገለፀው በወንዶችና በሴቶች መካከል ካለው ሥነሕይወታዊ ልዩነት ይልቅ ማህበረሰቡ በረጅም ጊዜ በፈጠራቸው ማህበራዊ ልዩነቶች ሳቢያ ሴቶች በኢኮኖሚ፣ በትምህርት፣ በሥነልቦና ዝቅ ተደርገው እንዲታዩ በመደረጉ ፣ በሴቶች ላይ ለሚደርሱ የሀይል ጥቃቶች አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡

አካላዊና ሥነልቦናዊ ጥቃቶች ሳቢያ ሴቶች በኑሮ የመጎሳቆልና የመገለል ችግር ስለሚደርስባቸው ከፍተኛ ችግር እያጋጠማቸው ነው ያሉት ጥናት አቅራቢዎቹ ይህንኑ ጉዳት ለማስወገድ ሴቶች በሕግ ረገድ ያላቸውን መብት እንዲረዱ ማድረግ ለመብታቸው እንዲቆሙ እንደሚያስችላቸውና በተጓዳኝም የሕብረተሰቡን ግንዛቤ በማዳበር ጉዳቱን በእጅጉ ይቀንሰዋል፡፡

አካላዊና ሥነልቦናዊ ጥቃቶች ሳቢያ ሴቶች በኑሮ የመጎሳቆልና የመገለል ችግር ስለሚደርስባቸው ከፍተኛ ችግር እያጋጠማቸው ነው ::



ሴቶች በልማት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ቢሆንም ፣ በዚሁ ማህበራዊ ልዩነት ሳቢያ በልማቱ ያላቸው ተሳትፎ በእጅጉ አናሣ መሆኑን ያመለከቱት ጥናት አቅራቢዎቹ ሴቶች በፆታቸው ምክንያት ብቻ በሚደርስባቸው ጫና መሠረታዊ ፍላጎታቸውን እንኳ ለማሟላት በሚያስችል ገቢ እጦት ሳቢያ በድህነት ውስጥ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

ይህንን በሴቶች ላይ የሚታየውን ድህነት ለመቀነስ የሥነፆታን ትምህርት አገራዊ የልማትና የዕድገት ፕሮግራም አድርጎ

በመቅረፅ መሥራት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል::

በዚሁ ለሁለት ቀናት በቆየው በፆታና ሥርዓተ ፆታ ፣ በቤተሰብ ህግ ፣ በሥነ-ተዋልዶና የጤና መብቶች ፣ በፅንስ ማቋረጥና በቤተሰብ ምጣኔ በተሰኙ ርዕሰ ጉዳዮች ጥናታዊ ጽሑፎች የቀረቡበት ዐውደ ጥናት ተሳታፊዎች በቡድን በርዕሰ ጉዳዮቹ ላይ ሠፊ ውይይት በማድረግ የጋራ ድምዳሜ ላይ መድረሳቸውንና ከፍተኛ ግንዛቤ እንዳስጨበጣቸው ገልፀዋል::

## በአፋር ክልል በጎርፍ አደጋ ተጎጂ ለሆኑ አስፈላጊው ዕርዳታ ቀርቧል



በዱብቲ ወረዳ በሚገኙ 5 ቀበሌዎች ውስጥ 800 የሚሆኑ አባዎራዎች ወይም 4000 ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል::

በአፋር ክልል በዱብቲ ወረዳ ሐምሌ 17 ቀን 1997 ዓ.ም በአዋሽ ወንዝ ሙላት ሳቢያ በተከሰተው የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ ተጎጂ ለሆኑ ወገኖች አስፈላጊው የምግብና የመጠለያ ዕርዳታ ቀርቧል::

የአደጋው መከሰት እንደተሰማ የደረሰውን ጉዳት መጠንና የሚያስፈልገውን ዕርዳታ ዓይነትና መጠን ለማጥናት ወደስፍራው የተንቀሳቀሰው የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ቡድን እንዳመለከተው ወንዙ ሞልቶ ከመውረጃ ገደቡ ውጭ በማጥለቅለቁ በዱብቲ ወረዳ ዴትባህሪ እና በያህሌ በተባሉ አካባቢዎች ጉዳት ማስከተሉን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናት ቡድን ሪፖርት አመልክቷል::

ቡድኑ በሪፖርቱ እንዳመለከተው በተጠቀሱት አካባቢዎች በሚገኙ 5 ቀበሌዎች ውስጥ 800 የሚሆኑ አባዎራዎች ወይም 4000 ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል:: በጎርፉ ሳቢያ በሰው ህይወት ላይ የሞት አደጋ አለመድረሱን ግን ለማረጋገጥ ተችሏል::

በዚሁ መሠረት በአደጋው ተጎጂ ለሆኑት ወገኖች በክልሉ በኩል 45 ካርቶን ብስኩት መከፋፈሉን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ፣ በሌላም በኩል ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን 80 ኩንታል ብስኩት እና 4 በ 50 ሜትር የሆኑ 10 ጥቅል የመጠለያ ኘላስቲክ ሽቶች ወደ ስፍራው ተጓጉዘዋል:: ከዚህም በተጨማሪ በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል በኩል 32 ካርቶን ብስኩት ለተጎጂዎቹ መቅረቡን ከስፍራው የተገኘው ሪፖርት ያመለክታል::

## የዕርዳታ እህል በግለሰብ መጋዘን ሲራገፍ ተያዘ

ለተረጂዎች እንዲጓጓዝ ከናዝሬት ማዕከላዊ መጋዘን የተጫነ የዕርዳታ እህል ሐምሌ 16 ቀን 1997 ዓ.ም በግለሰብ መጋዘን ሲራገፍ እጅ ከፍንጅ ተይዟል::

ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የንብረት አስተዳደርና ትራንስፖርት ማስተባበሪያ መምሪያ የደረሰን ዘገባ እንደሚያመለክተው አቶ ጴጥሮስ ገዛኸቃ የተባለ አሽከርካሪ በመጠየቂያ ቁጥር 273577 ለሱማሌ ክልል አፍዴር ዞን በባ ወረዳ ለሚገኘው ሌልርሁር የተባለ ማራገፊያ ጣቢያ ለሐምሌ ወር ከተጠየቀው 596 ኩንታል ስንዴ ውስጥ 200.9 ኩንታል ወይም 400 ከረጢት ሐምሌ 16 ቀን 1997 ዓ.ም በወጪ ሰነድ ቁጥር 048938 የሠሌዳ ቁጥሩ 3-26872 በሆነ የጭነት ማጓጓዣ ተሽከርካሪ

ጭኖ ከወጣ በኋላ በዛው በናዝሬት ከተማ በአንድ ግለሰብ መጋዘን ውስጥ ሲያራግፍ በህብረተሰቡ ጥቆማ እጅ ከፍንጅ ሊያዝ ችሏል።

የችግሩ መከሰት እንደተሰማም ኮሚሽኑ ወዲያውኑ ጉዳዩን ለፌዴራል ፖሊስ በማሳወቅ መርማሪ ፖሊሶች ወደተጠቀሰው ሥፍራ እንዲንቀሳቀሱ ተደርጎ የፌዴራል ፖሊስ አባላቱ ተገቢውን ምርመራ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

በዚህ አጋጣሚ ኮሚሽኑ ለተረጂ ወገኖቻችን የሚልከውን የዕርዳታ እህል በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለግል ጥቅማቸው ለማዋልና በተረጂው ህዝብ ላይ ከፍተኛ ደባ የሚፈጽሙ ግለሰቦችን በማጋለጥ ህብረተሰቡ የተለመደ ትብብሩን እንዲቀጥል አመዝኮ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ኣመዘኮ